የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ቁጥር ፱
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No.9
ADDIS ABABA ,25th December, 2025

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፰/፪ሺ፲፰

ዘላቂ እና ንፁህ የኢነርጂ ተደራሽነት ለውጥን ለማፋጠን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ……………………………………………………………………ገጽ ፲፱ሺ፬፻፴፯

## Content

Proclamation No.1398/2025

International Development Association Loan Agreement for financing Accelerating Sustainable and Clean Energy Access Transformation program Ratification Proclamation……............................ Page 19437

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፰ /፪ሺ፲፰

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ዘላቂ እና ንፁህ የኢነርጂ ተደራሽነት ለውጥን ለማፋጠን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ሁለት መቶ ዘጠና አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ኤስዲአር (፪፻፺፬ ሚሊዮን ፱፻ ሺ ኤስዲአር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል ነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1398 /2025

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS**, the Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association stipulating that International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to two hundred ninety four million nine hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 294,900,000) for financing Accelerating Sustainable and Clean Energy Access Transformation program was signed on the 15th day of August 2025;

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም በ፫ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ዘላቂ እና ንፁህ የኢነርጂ ተደራሽነት ለውጥን ለማፋጠን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፰/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል ነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7901-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሁለት መቶ ዘጠና አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ኤስዲአር (፪፻፺፬ ሚሊዮን ፱፻ ሺ ኤስዲአር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS**, the House of Peoples Represenatative of the Federal Democratic Republic of Ethiopian has ratified the said loan agreement at its 3rd regular session held on 4th day of December 2025;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing Accelerating Sustainable and Clean Energy Access Transformation program Ratification Proclamation No. 1398/2025".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Credit Number 7901-ET signed on the 15th day of August 2025 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Two Hundred Ninety Four Million Nine Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 294,900,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አፅቀስላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 25th Day of December ,2025**

**TAYE ATSKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**